# ንፋስ በነፈሰው መጓዝ እስከ መቼ ?

## ከሃብሮማይ

ታዋቂው እንግሊዛዊ ፖለቲከኛ ኤድመንድ ብሩክ "ተቃዋሚዎች ነርቫችንን ያነቃቃሉ፣ ችሎታችንንም ይስላሉ፣ የሚቃወሙን የሚያግዙን ናቸው" ብሏል፡፡ በእርግጥም በብሔራዊ ጉዳይ ላይ ስምምነት የደረሱ (national consensus) ያላቸው አገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቃወሙት ከራሳቸው ፍላጎት ተነስተው ሳይሆን ከአገራቸው ጥቅም ተነስተው ነው፡፡ ስለዚህም አፈርድሜ ከማብላት ይልቅ ደካማ ጎንን ማሳየት፣ መሻሻል የሚገባቸውን መጠቆምና ከሁሉ በላይ
አብሮ ለመሥራት መነሳሳት ይታይባቸዋል፡፡ በተግባርም ይገልፁታል።

አንድ አገር ጠንካራ የዲሞክራሲ ግንባታ ለማካሄድ ከፈለገች ብዙህነትን (pluralism) መቀበል ይኖርባታል፡፡ አገሮች የተለያየ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ባህል፣ እምነት፣ ወግ፣ ቋንቋ ወዘተ...ስላላቸው ከዚህ በመነጨ የተለያዩ ፍላጎቶች መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ የተለያየ ቋንቋ፣ እምነት ...የሌላቸው ወይም አንድ ዓይነት ሃይማኖትና ቋንቋ ያላቸው አገሮችም አንድ ዓይነት ፍላጎት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም እንደ አገር እንተወውና እንደ ቡድንም ግለሰብም የተለያዩ ፍላጎቶች አሉን፡፡ ስለሆነም ነው ለአንድ አገር ዲሞክራሲ ብዙህነት ምሰሶ ነው የሚባለው፡፡

ብዙህነትን መቀበል ማለት ዞሮ ዞሮ የተለያዩ ፍላጎቶችን በዲሞክራሲያዊ አኳሃን ማስተናገድ ማለት ነው፡፡ እነዚህን ፍላጎቶች ለሟሟላት ደግሞ የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መፈጠራቸው አይቀርም፡፡ የነዚህ ፓርቲዎች ዋና ዓላማ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በህዝብ የተመረጠ መንግስት ያሉትን ጠንካራ ጎኖች ከመንግስት ጎን ሆነው አብረው

የሚያጠናክሩበት፤ ደካማ ጎኖች ካሉት ደግሞ የሚያሳዩበትና የሚተቹበት በአጠቃላይ በአገራዊ ጉዳይ ላይ በፖለቲካ ሕግ ጨዋታ የሚፋጩበት መድረክ
ነው፡፡ መንግስትም ችግሮቹን አይቶ የማስተካከል እርምጃ የሚወስድበት ጭምር፡፡

ይህ ሊሆን የሚችለው መንግስትና ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ የሚያደርጋቸውና የሚያስማማቸው ጉዳይ ካለ ነው ፡፡አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ከሌለ ስለ ጋራ ጉዳይ ማሰባቸው ይቀራል፡፡ነገር ግን በዲሞክራሲ የዳበሩ አገራት መንግስትም ተቃዋሚ ፓርቲዎችም አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ አለ፡፡እሱም በህዝባቸው ተሳትፎ እውን የሆነ ቃል ኪዳናቸው ሕገ መንግስታቸው ነው፡፡

ስለሆነም በጨዋታው ሕግ መሠረት ምንም ቢፋጩና ቢተቻቹም በአገራቸው ደህንነት ጉዳይ ግን የጋራ የሆነ ስምምነት አላቸው፡፡ሕገ መንግስታቸው የሁሉም ሕጎች የበላይ መሆኑን ከመቀበል ባሻገር መንግስትም ተቃዋሚዎችም ያለ ምንም ማመንታት ይህንኑ ያከብራሉ፤ ያስከብራሉ፡፡

እንዲህ ስለሆነም ነው እንግሊዛዊው ገጣሚ ዊልያም ብሌክ በመፅሐፉ ስለ ተቃዋሚዎች ሲገልጽ “መቃወም ጥሩ ጓደኝነትን ይፈጥራል” ብሎ የተናገረው፡፡ ሌላው እንግሊዛዊ ፖለቲከኛ (English state man) ወይም አመራር ላይ የነበረ ኤድመንድ ብሩክም “ተቃዋሚዎች ነርቫችንን ያነቃቃሉ፤ ችሎታችንም ይስላሉ፤ የሚቃወሙን የሚያግዙን ናቸው” ያለው፡፡ በእርግጥም በብሔራዊ ጉዳይ ላይ ስምምነት ያላቸው አገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚቃወሙት ከራሳቸው ፍላጎት ተነስተው ሳይሆን ከህዝባቸውና አገራቸው ጥቅም ተነስተው ነው፡

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማውን፣ ፖሊሲውንና ስትራተጂውን ለህብረተሰቡ በሚገባ ካስታወቀ ህብረተሰቡ የሚጠቅመውን ፓርቲ ለመለየት በርይከፍትለታል፡፡ስትራተጂካዊ ራእይ የሌለው ፓርቲ ከሆነ ግን ድፍን፣ የሚቃወም ፓርቲ ስለሚሆን ምንም እንኳ በህጉ መሰረት ፓርቲ የመመስረት መብት ይኑረው እንጂ ለህብረተሰቡ ግን ሚያመጣው ፋይዳ የለውም- ከስሜታዊነት ከዚያም አልፎ ከሁከትና ብጥብጥ ውጪ፡፡ፓርቲዎች ለቆሙለት ዓላማና የህብረተሰብ ክፍል በዴሞክራሶያዊ አኳሃን በመታገል ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ባሻገር አላማቸውን ማራመድ የሚችሉት የዴሞክራሲ ስርዓት ሲገነባ መሆኑን በመገንዘብ የዴሞክራሲ ባህል እንዲያብብ፤የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው አያጠያይቅም፡፡

የአገራችን የፖለቲካ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከላይ እንደተገለፀው ዴሞክራሲያዊ የሆነ ባህሪ ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡እነዚሁ ፓርቲዎች አንድ የፖለቲካ ዓላማን ለማራመድ፤በዚህ የፖለቲካ ዓላማ ለመሰባሰብ የሚፈልጉ ዜጎችን በሙሉ ለማሰባሰብ የሚጥሩና መነሻ መድረሻቸው ዓላማቸው ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ዓላማዎቻቸውን ለማራመድ ዓላማቸውን ራሱ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባቸው ነበር፡፡ከዚህም ባሻገር ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን በመተንተንና በማቀናበር ለህዝብ የማቅረብ አቅም ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡ነገር ግን እስካሁን ባለው አካሄዳቸው በተግባር እንተወውና በንድፈ ሃሳብም የዴሞክራሲ ምንነት የተረዱ አይመስለኝም፡፡

እንደዚህ ዓይነቱን የፖለቲካ አመራር ለመስጠት የማይችል ፓርቲ ደግሞ አንድም የፖለቲካ ፓርቲ ሊሆን አይችልም፤አለበለዚያም ተልእኮውን በአግባቡ ሊወጣ የሚችል ፓርቲ አይደለም ፡፡ ፓርቲዎቹ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተላበሱ ሁነው አይታዩኝም፡፡አመራሮቹ ራሳቸው በራሳቸው በሚያደርጉት ስብሰባ እንኳን ሲሰዳደቡ፤የመደማመጥና የመቻቻል ባህልም ድምጥምጡን ሲያጠፉት ነው የሚታዩት፡፡እነዚህ

ፓርቲዎች ልዩነትን እንደ ጌጥ ከማየት ይልቅ በመሰዳደብ ሊፈቱት ከሞከሩ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና፣ባህሎች፣ቋንቋዎች...ወዘተ ባለቤት ለሆነችና የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉባት አገራችን በሰለጠነ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንዴት ብለው ነው ሊመሯት የሚችሉ?

እነዚህ ፓርቲዎች ባለፉት ጊዚያት የነበራቸውን አካሄድ ስገመግመው ለህገ መንግስቱ የበላይነትን በአስተማማኝ ደረጃ የሚያከብሩና የሚያስከብሩ ሆነው አልታዩኝም፡፡ምክንያቱም መንግስት ስርዓትን የማስከበር ሃላፊነት እስካለው ድረስ ማናቸውም ሕግ ተላልፏል ያላቸንውና ሕገመንግስታዊ ድንጋጌውም በግልጽና በማያሻማ መንገድ የጣሱ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት ሲያቀርባቸው፣ተቃዋሚዎቹ ለሕግ የበላይነትን ለማስከበር ሕገ ወጦችን ከማውገዝ ይልቅ ለሕገ ወጦችን መደገፍና መወደስ እንደ ዋነኛው መለያቸው ሆነዋል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባህሪያቸው ሁሉ ለአናርኪዝም (anarchism) የተመቸ ሆነዋል ካልኩ የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡የቀድሞ የፈረንሳይ ታዋቂ ፖለቲከኛና አናርኪዝምን ከጻነሰሱ ዋነኛዎቹ ተብለው ከሚነገርላቸው አንዱ ጆሴፍ ፕሮድሃን ስለ አናርኪዝም ሲገልፅ “አናርኪዝም ማለት አንድ አገር መንግስት አያስፈልጋትም፣አገሪቷ ያለ ሕግና ያለ ስርዓት መንቀሳቀስ አለባት፣ማንኛውም ሰው ለራሱ በመሰለው ሁሉ የሌላውን መብት ግምት ውስጥ ሳያስገባ እንደፈለገ መፈንጨት አለበት” ይላል፡፡የኛ አገር የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ደግሞ ሕገ መንግስቱን ለመናድና መንግስትን በሃይል ለመጣል በተካሄደው ሴራ ተሳትፈው ህይወታቸውን ያለፉ ሰዎች ሕገ ወጥነታቸውን በማወደስ “ሰማዕታት” በማለት መኢአድና አንድነት ፓርቲዎች መዘከራችው፣ ሕገ መንግስቱ ለመናድ ከሞከሩና እድሜ ልክ እስራት ከተፈረደባቸው ከዚያም በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ይቅርታ የተደረገላቸው አንዷ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ይቅርታ አልጠየቅኩም በማለታቸው በሕጉ መሰረት የተሰጣቸውን ይቅርታ እንዲነሳ ተደርጎ ወደ ማረምያ ቤት በመግባታቸው ፣ የአገራችን ተቃዋሚዎች ወንጀለኛዋ

በማወደስና በማሞገስ የ 5ኛ ወር እስራት መዘከርያ በሚል የመኢአዱ መሪ ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል በተገኙበት ማክበራቸው፤በቅርቡ የወጣው የአገራችን የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅ በሰፊው መኮነናቸው ከዚያም አልፈው ሕጉ ራሱ “ሽብር” ነው ማለታቸው፤ቀቢጸ ተስፋ የሽብር ቡድን በአገራችን ሽብር ለመፍጠር ሲሞክር በቁጥጥር ስር በመዋሉ ደስ ሊላቸው ሲገባ ፤የኦፍዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ እኔ የቡዱኑ መሪ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ካልነገረኝ አላምንም ብለው መናገራቸውና ከመንግስትና ህዝብ በላይ አሸባሪዎችና ሕገ ወጦችን እንደሚያምኑ በይፋ መናገራቸው…ወዘተ ሲታይ ተቃዋሚዎች ከባህሪያቸውና ድብቅ አጀንዳቸው ብሎም ከሕገ ወጥነታቸው የተነሳ ወንጀልነትን የማውገዝ ልምንድም ሆነ ባህሪይ እንደሌላቸው በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም እነዚህ የአገራችን የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ሕገ ወጥነትን እያበረታቱ አገራችን ወደ ስርዓት አልበኝነት ለመውሰድና ማንኛውም ሕገ ወጥ እንደፈለገ መሆን አለበት የሚል ዓይነት አዝማምያ ያለው አካሄዳቸው ለአናርኪዝም የተመቸች አገር ለማድረግ ጥረት እያደረጉ መሆናቸው በግልፅ የሚያሳይ ነው ፡፡

ሌላም በ ምርጫ 97 ጊዜ ህዝቡን በሰጠው ድምጽ ከመተማመንና በሰለጠነ አኳሃን አሜን ብሎ ከመቀበል ይልቅ አና ጎሜዝን ይዘን የማንደርስበት የስልጣን ደረጃ የለም ብለው አምነው ነበር፡፡ ሊሆን አልቻለም፡፡ አልሆነምም፡፡ ለወፊትም ታዛቢ ታዛቢ
ነው፡፡ መራጭ ሕዝብ ምን ጊዜም መራጭ ሕዝብ ነው፡፡የፖለቲካ መድረኩ ስፋት ለህዝቦቻችንና በህዝቦቻችን ለሚመሩት ተቋሞቻችን ነው እንጂ ለማንም የውጭ ዜጋም አይደለም፡፡ይሁን እንጂ አሁንም ካለፈው ተሞክራቸው ሊማሩ የቻሉ አይመስለኝም፡፡ በአሁኑ ወቅት አንድነትን የመሰሉ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ እንግሊዝ ኤምባሲ በመሄድ መጪውን ምርጫ ላይሳተፉ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ በግልጽ እየተናገሩ ነው ያሉት፡፡እኔኮ የሚገርመኝ ለምንድነው

ተቃዋሚዎቻችን በኢትዮጵያ ህዝብ ከመተማመን ይልቅ በውጭ ዜጎች የሚያምኑት? የቀድሞው የአሜሪካ ፕረዚዴንት አብርሃም ሊንከን ስለ ዴሞክራሲ ሲናገር ዴሞክራሲ ማለት በህዝብ፤ከህዝብ፤ወደ ህዝብ ነው አላለም እንዴ? እንደኔ አመለካከት እነዚህ ሰዎች ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ትግል ዝግጁ እንዳልሆኑ ከምርጫ 97 ብንማርም በዛን ጊዜ በሰሩት ስራ ተፀጽተው በተሰጣቸው በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ይቅርታ መሰረት በሰለጠነ የዴሞክራሲ አካሄድ ለመሄድ ዝግጁነት የሌላቸው ናቸው፡፡ትኩረታቸው ሁሉ ከአገራችን ህዝብ ይልቅ የውጭ ኢምባሲዎችና ሌሎች ከሆነ ፤የውጭ አገራት አምባሳደሮችና መንግስታትን እንደ ጌቶቻቸው ከቆጠሯቸው እነዚህ ፓርቲዎች
ከአገር ደህንነት አኳያ የማያስተማምኑ ከመሆናቸው ባሻገር አንድም ህዝባዊ መሰረት የሌላቸው፤ ሌላም ፀረ ዴሞክራሲ ናቸው ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ የኛ አገር የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ግልፅ የሆነ (አንዳንዱ ጭራሽ ያለመኖር) የፖለቲካ ፕሮግራም አለመያዝ፣ ሽንፈትን በፀጋ አለመቀበል፣ የመቻቻል አቅም ዜሮ መሆን፣ አደገኛ የፕሮፓጋንዳና የኮሚዩኒኬሽን ስልት፤ሂስና ነቀፌታ ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣ ልዩነትን ወደ ጥላቻ መቀየር፣ አባልን በዓላማ ከማሰባሰብ በስሜትና ባልሆነ መረጃ ማቅረብና ማራቅ፣ በገንዘብ ዙሪያ ምግባረ ብልሹነት፣ እርስ በርስ መወነጃጀል ወዘተ. መለያቸው ሆነዋል፡፡

እዚህ ላይ ተቃዋሚዎች ለምንድነው ይህንን የሚያደርጉት? ለምንድነው እስካሁን ግልፅና አማራጭ የሚሆን ፖሊሲና ስትራተጂ ማቅረብ የተሳናቸው? ብለን መጠየቁ ተገቢ ነው፡፡

የአገራችን ተቃዋሚዎች በአገራችን ህዝቦች ፍላጎት እውን በሆነው ህገ መንግስታችን ያላቸው እምነት አናሳ ስለሆነ ነው፡፡ በመግቢያዬ አካባቢ እንደገለፅኩት አገር አንድ የሚያደርጋት የጋራ መግባባት ያስፈልጋታል፡፡ ይህ ብሔራዊ መግባባት የሚመጣው ደግሞ ሕገ መንግስቱን በማክበርና

በማስከበር ነው፡፡የአገራችን የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ግን ከጀርባቸው ደብቀውት ያሉት ጩቤ በግልፅ በፖሊሲያቸውና ስትራተጂያቸው ካወጡት በህዝባችን ምን እንደሚደርሳቸው ስለሚያውቁ ግልፅ ከሆነ አካሄድ ተቆጥበው ንፋስ በነፈሰበት ሁሉ መሄድ መርጧል፡፡

ከዚህ ይዘውት ያሉት አስተሳሰብ ወጥተው የሕገ መንግስቱን ፍፁም የበላይነት ተቀብለው፤በውጭ ዜጎች ከመተማመን ወጥተው በዜጎቻቸው የሚተማመኑበትና ከህገ ወጥ ትግላቸው ወደ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ትግል የሚመጡበትና በሰፊው የፖለቲካ ምህዳር የሚጋልቡበት ፤ከኋላቸው ተደብቆ ያለውን ጩቤ አሽቀንጥረው የሚጥሉበት ጊዜ ይኖር ይኾን?